**የሕገ-መንግሥት መብት ድል ወይስ የሥነ-ሥርዓት አጣብቂኝ?፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ባለሰባት ዳኞች ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 236212 ጥር 25 ቀን 2018 ዓ/ም በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለውጥ ላይ የቀረበ ሂሳዊ ትንታኔ**

**በአቶ አልማው ወሌ**


***የጽሑፉ ጭምቅ ሃሳብ***

*የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ለረጅም ጊዜ ሲያከራክር የኖረ አንድ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት አጣብቂኝ (Procedural Paradox) አለ፡- እሱም የፍርድን የመጨረሻነት (Finality of Judgments) መሠረታዊ መርህ ሳያፈርሱ፣ በክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ ባልነበረበት ሁኔታ ንብረቱ በፍርድ አፈጻጸም ለሌላ ሰው የተላለፈበትን የሦስተኛ ወገን ፍትሕ የማግኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብት እንዴት ማስከበር ይቻላል? የሚለው ነው፡፡ ለዓመታት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሁለት ጽንፎች መካከል ሲዋልል ቆይቷል፤ ወይ ከፍርድ አፈጻጸም በኋላ አዲስ ክስ ማቅረብን ያለምንም ገደብ መፍቀድ (በሰ/መ/ቁ 50835)፣ አሊያም የሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍናን (procedural economy) ሰበብ በማድረግ ፍጹም ክልከላ ማድረግ (በሰ/መ/ቁ 67127)፡፡ በቅርቡ በሰ/መ/ቁ 236212 በሰባት ዳኞች የተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ "በቅድመ-ሁኔታ የታጠረ የልዩ ሁኔታ መብት" (Qualified Exception Rule) በማስተዋወቅ ይህንን የሕግ ስብራት ለመጠገን ሞክሯል፡፡ ይህ ጽሑፍ የዚህን ታሪካዊ ውሳኔ አይነታዊ፣ ሕገ-መንግሥታዊ እና ተግባራዊ ገጽታዎች በጥልቀት ይተነትናል፡፡ ችሎቱ ፍላጎቶችን ሚዛናዊ ወደማድረግ (balancing-of-interests) የተጓዘበትን የትንታኔ ዘዴ ጽሑፉ የሚያደንቅ ቢሆንም፣ አዲስ ክስ ለማቅረብ የተሰጠውን መብት ጥብቅ ከሆነ የ"ከአቅም በላይ የሆነ" (force majeure) ወይም "በቂ ምክንያት" የማስረዳት ሸክም ጋር ማስተሳሰሩ፣ መሠረታዊ የሆኑ ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችን በተግባር ሊያኮላሽ የሚችል አደገኛ የማስረጃ ሸክም መፍጠሩን ይሞግታል፡፡*


## ፩. መግቢያ፡- የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ዋነኛ ፈተና

በማንኛውም ውጤታማ የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር እምብርት ውስጥ፣ ሁልጊዜም እርስ በርስ የሚፋጠጡ ሁለት የሕግ መርሆዎች አሉ፡፡ እነዚህም ከመሰማት መብት ጋር የተያያዘው የሌላኛውን ወገን ስማ የሚለው መርህ እና ከህዝብና ከመንግስት ፍላጎት/ፖሊሲ አንጻር ክርክሮች ማብቂያ ሊኖራቸው ይገባል የሚለው መርህ ናቸው፡፡፡

በአገራችን የፍትሃ ብሔር ፍትህ ስርዓት ውስጥ ይህ ፍጥጫ አብዛኛውን ጊዜ ጎልቶ የሚወጣው፣ ሦስተኛ ወገኖች መጥሪያ ባልደረሳቸው እና ባልተሰሙበት ክርክር ላይ ተመሥርቶ በሚሰጥ ፍርድ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረታቸው በአፈጻጸም ተከብሮ ለፍርድ ባለመብቶች ተላልፎ ሲያገኙት በሚፈጠር ሁኔታ ነው፡፡ በ1958 ዓ.ም የወጣው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በቁጥር 358 ድንጋጌ ሥር "የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ" መብትን የደነገገ ቢሆንም፣ የዚህን ድንጋጌ ተፈጻሚነት "ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት" በሚል የጊዜ ገደብ አጥብቦታል፡፡ እንዲህ ከሆነ የፍርድ አፈጻጸሙ ከተጠናቀቀ በኋላ ምን ዓይነት የሕግ መፍትሔ ይኖራል? ይህ የሕግ ክፍተት በሰበር ሰሚ ችሎት ዘንድ እርስ በርሱ የሚቃረን የአስገዳጅ የህግ ትርጉም (Conflicting interpretative binding Precedent) እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡ በቅርቡ በሰ/መ/ቁጥር 236212 የተሰጠው ውሳኔ የዚህን ክፍተት አቅጣጫ የቀየረ ታሪካዊ ክስተት ነው ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ችሎቱ የሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍናን ከሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 (ፍትሕ የማግኘት መብት) ጋር የማስታረቅ ከባድ ኃላፊነት የወሰበደበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ነው፡፡ ይህ አጭር

ጽሑፍ የችሎቱን የሕግ ትንታኔ ዘዴ (methodology)፣ የንጽጽራዊ ሕግ መሠረቶችን፣ እና አዲሱ መርህ በተግባር የሚያመጣቸውን ውጤቶች በጥልቀት ይተነትናል፡፡

፪. አይነታዊ/ዶክትሪናል/ ትንታኔ፡-በፍርድ ስለማለቅ እና የፍርድ መጨረሻነት

የሰ/መ/ቁ 236212 ውሳኔን ትክክለኛ ውጤቱንና በአገሪቱ የዳኝነት ስርዓት ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን ክብደት ለመረዳት መጀመሪያ ትርጉሙ ሊፈታው የሞከረውን የአስገዳጅ የህግ ትርጉም አሰጣጥ ቀውስ መገንዘብ ያሻል፡፡

ቀድሞ በፍርድ ማለቅ /ሪስጁዲካታ/ በሚባለው መሠረታዊ መርህ መሠረት አንድ ውሳኔ አስገዳጅ የሚሆነው በተከራካሪ ወገኖች እና መብት በተላለፈላቸው ሰዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ችሎቱም ይህንኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 5 ድንጋጌ ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቅ ጉዳይ መሆኑን በትክክል አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ውጭ የክርክሩ ተካፋይ ባልነበረበት ክርክር በተሰጠ ውሳኔ ንብረቱን የተነጠቀ ሦስተኛ ወገን፣ ከሕግ አግባብ ውጭ (without due process) ንብረቱን አጥቷል ማለት ነው፡፡ ይሁንና ይህን መብት ለማስከበር በሚል፣ ከፍርድ አፈጻጸም በኋላ ሦስተኛ ወገኖች ማለቂያ የሌለው "አዲስ ክስ" በተፈጸሙ ጉዳዮች ላይ እንዲያቀርቡ መፍቀድ ደግሞ የፍርድን የመጨረሻነትና ቅድስና/አሳሪነት ትርጉም አልባ የማድረግ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው አዲስ ውሳኔ በፊት ሰበር ሰሚ ችሎቱ ሁለት እርስ በርስ የሚጣረሱ አስገዳጅነት ያላቸውን የህግ ትርጉሞችን ሰጥቶ ነበር፡፡

አንዱ አስገዳጅ የህግ ትርጉሙ በሰ/መ/ቁጥር 50835 ላይ የተሰጠው ሲሆን ይህ ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ያልነበረ 3ኛ ወገን አዲስ ክስ በማቅረብ መብታቸውን ለማስከበር ምንም አይነት ገደብ ያላደረና አዲስ ክስ ማቅረብን ያለምንም ገደብ የሚፈቅድ አቋም ችሎቱ መያዙን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ አገላልጽ ይህ ውሳኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418፣ 421 እና 455 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ሦስተኛ ወገኖች ከአፈጻጸም በኋላ አዲስ ክስ ማቅረብ ይችላሉ የሚል አቋም ችሎቱ ይዞበት የነበረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 236212 የተሰጠው አዲሱ የህግ ትርጉም ላይ ችሎቱ በትክክል እንደተቸው በሰ/መ/ቁጥር 50835 በችሎቱ የተንፀባረቀው የሕግ አተረጓጎም ስህተት ነበር፡፡ እነዚያ ድንጋጌዎች በአፈጻጸም ንብረት በሚከበርበት (attachment) ጊዜ የሚቀርቡ እንጂ፣ የመጨረሻ እልባት ያገኘን ዋና የፍርድ ውሳኔ ሽሮ አዲስ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ አይደሉም የሚል ክርክር ሊነሳባቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ ሌላው በሰ/መ/ቁጥር 67127 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሁኖ ይህ ትርጉም ደግሞ ፍጹም ክልከላ የሚያደርገው የችሎቱ አቋም የተያዘበት ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ትርጉም የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ድንጋጌን በንባቡ ላይ ብቻ (textualist reading) በመመሥረት በሚመስል መልኩ አንዴ ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ የፍትሕ በሮች ለዘላለም ይዘጋሉ የሚል አቋም ተይዞበት የነበረ መሆኑን የውሳኔው ሙሉ ይዘት ያሳያል፡፡ ቅርብ ጊዜ በሰ/መ/ቁ 236212 ችሎቱ የያዘው የህግ ትርጉም አቋም በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ እነዚህ ሁለቱም ጽንፈኛ አቋሞች የሕግን መሠረታዊ ዓላማ እንደሚያስቱ በትክክል ለመገንዘብ ጥረት ያደረገ ይመስላል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው አቋም (ያለገደብ አዲስ ክስ መፍቀድ) የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የመጨረሻነት (Finality of Judgment) ትርጉም አልባ በማድረግ በፍትሕ አስተዳደሩ ላይ ማለቂያ የሌለው ትርምስን (chaos/multiplicity of suits) የሚፈጥር ሲሆን፤ ሁለተኛው አቋም (ፍጹም ክልከላ ማድረግ) ደግሞ የሥነ-ሥርዓት ሕግን ድንጋጌ ሽፋን በማድረግ ዜጎች ንብረታቸውን በሕግ አግባብ የመከላከል እና የመሰማት ሕገ-

መንግሥታዊ መብታቸውን አጥተው በሕግ ስም ግፍ (legalized injustice/tyranny) እንዲፈጸምባቸው ሊያደርግ ይችላል የሚል ግንዛቤ የተያዘበት ሁኖ ይታያል፡፡

**፫. የችሎቱ የትንታኔ ዘዴ፡- ግብ-ተኮር ትርጉም እና ሕገ-መንግሥታዊ ሚዛን**

የሰ/መ/ቁ 236212 ውሳኔ ዘዴያዊ (methodological) ብልሃት የሚታየው ቃል በቃል ሕግን ከመተርጎም ወጥቶ ግብ-ተኮር (teleological) እና ሕገ-መንግሥታዊ ሚዛንን የመጠበቅ አካሄድ መከተሉ ይመስለኛል፡፡

ችሎቱ የሥነ-ሥርዓት ሕጎች በራሳቸው ግብ ሳይሆኑ መሠረታዊ ፍትሕን ለማምጣት የሚያስችሉ መሣሪያዎች መሆናቸውን ያመነ ሁኖም ታይቶኛል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ድንጋጌን ዋቢ በማድረግ ችሎቱ ክርክሩን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ተራ የንባብ ትርጉም አውጥቶ ወደ ሕገ-መንግሥታዊ የፍትሕ ሂደት (due process) ከፍ ያደረገው መሆኑንም ውሳኔው ያስገነዝባል፡፡ አንድ ዜጋ የመሰማት ዕድል ሳያገኝ መሠረታዊ የሆነ የሕገ-መንግሥት መብቱን (የንብረት መብት) እንዲያጣ የሚያደርግ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ትርጉም በባህሪው እንከን ያለበት መሆኑን ችሎቱ በውሳኔው ውስጥ በሚገባ አስረድቷል፡፡ ከዚህያም በኋላ ቁልፉ የህግ ትርጉም/Ratio decidendi/ ክፍሉ ችሎቱ "በቅድመ-ሁኔታ የታጠረ የልዩ ሁኔታ" መብት (The "Qualified Exception" Rule) ይዞ ብቅ ማለቱን ውሳኔው ያስገነዝባል፡፡ በሌላ አገላለፅ ችሎቱ በቁልፉ የውሳኔው ክፍል አዲስ የሕግ ዶክትሪን አስቀምጧል፡፡ ይኸው አንድ ሦስተኛ ወገን ፍርድ ከተፈጸመ በኋላ አዲስ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው ከአቅም በላይ በሆነ አሊያም *በቂ በሆነ ምክንያት* ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መብቱን የሚነካ ውሳኔ ስለመኖሩ ማወቅ አለመቻሉን ወይም በተመሳሳይ ምክንያት የመቃወም አቤቱታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ. 358 መሠረት አለመቻሉን ማስረዳት ሲችል ብቻ ነው የሚለው መርህ ነው፡፡

ይህ "በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ልዩ መብት" ነው፡፡ በችሎቱ የተበጀተው ይኸው ዳርድንበር ሥርዓቱን በሚገባ ለማጣጣም ጥረት መደረጉን ያስገነዝባል፡፡ በአንድ በኩል የተፈጸመው ፍርድ የመጨረሻነት ግምት (presumption of finality) እንዲኖረው ያደርግና በሌላ በኩል ግን ይህ ግምት ተቀባይነት ባለው ከፍተኛ የማስረዳት ሸክም (excusable ignorance) ሊሰበር የሚችል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

**፬. የችሎቱ አዲስ ትርጉም/መርህ/ በዘመናዊ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ግቦች እና በኢትዮጵያ ሕግ ማዕቀፍ አንጻር ሲመዘን**

በዚህ የዳኝነት ትንታኔ ውስጥ መታለፍ የሌለበት እጅግ ወሳኝ ነጥብ፣ አስገዳጅ ትርጉሙ ከዘመናዊ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት አስተዳደር ግቦች ጋር ያለው ስምምነት ነው፡፡ እንደ ሎርድ ዎልፍ (Lord Woolf) ያሉ ታላላቅ የዘመናዊ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ሊቃውንት እንደሚገልጹት፣ የማንኛውም ውጤታማ የሥነ-ሥርዓት ሕግ "ቀዳሚ ዓላማ" (Overriding Objective) ጉዳዮችን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ፣ በተመጣጠነ ወጪ እና አላስፈላጊ መዘግየትን በማስወገድ እልባት መስጠት ነው፡፡ ፕሮፌሰር አሌን ሴድለር በ1958 ዓ.ም የኢትዮጵያን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ላይ በጻፉት መፅሐፍ ውስጥም ሕጉ ከዘረጋቸው ዋነኛ ፍልስፍናዎች አንዱ "የክስ መብዛትን መከላከልና" (prevention of multiplicity of suits) በአንድ ጉዳይ ላይ የተሟላ ፍርድ መስጠት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይህም በህጉ አንቀጽ 36፣ 40 እና 43 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚገኝ ሲሆን ሰበር ችሎቱም በተለያዩ መዛግበት የስነ ስርዓት ህጉን አይነተኛ ዓላማዎችን በመጥቀስ ውሳኔ ሰጥቶ ይገኛል፡፡

የሰበር ችሎቱ በአዲሱ ውሳኔው የዘመናዊውን ሥነ-ሥርዓት ግብ በሚገባ ተንትኗል፡፡ ችሎቱ እንዳስቀመጠው የተፈጸሙ ፍርዶች እንደገና እንዲከፈቱ መፍቀድ "የውሳኔዎችን ወጥነት እና ተገማችነትን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል" እንዲሁም "ክርክሮች ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡" ይሁንና ዘመናዊ የሥነ-ሥርዓት ቅልጥፍና (procedural efficiency) ማለት መዝገቦችን በቶሎ መዝጋት ማለት ብቻ አይደለም፤ እውነተኛና ፍትሐዊ የክርክር አፈታት መፍጠር ማለት እንጂ፡፡

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሥርዓት ውስጥ ያለው መሠረታዊ ማነቆ፣ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርብ ገና ከጅምሩ አግባብነት ያላቸውን ወገኖች አጣርቶ የማካተት (pre-trial case management) ደካማነት ነው፡፡ ይህ የፊት-ለፊት ክፍተት ችሎቱ ችግሩን በፍርድ አፈጻጸም መጨረሻ ላይ (back-end) እንዲፈታ አስገድዶታል፡፡ ስለዚህ፣ ችሎቱ "አዲስ ክስ ማቅረብ ያልተገደበ ሳይሆን..." በማለት ቅድመ-ሁኔታ ማስቀመጡ፣ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን "ቅልጥፍና እና የፍርድ የመጨረሻነት" (efficiency and finality) ግብ ከማክበሩም በላይ፣ ሥርዓቱን ከማይረቡ እና አላስፈላጊ ከሆኑ) የድህረ-አፈጻጸም ክሶች የታደገበት እርምጃ ዘመናዊ የፍትሕ አስተዳደር መርሆዎችን የተከተለ ነው ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

## ፩ የንጽጽራዊ ሕግ ዳሰሳ፡- የሦስተኛ ወገን መብቶችን ማስተናገድ

የሰበር ችሎቱ የገጠመው ፈተና ለኢትዮጵያ ብቻ ያለ አይደለም፡፡ የአገራትን ንጽጽራዊ ቅኝት ስናደርግ የአገራችን ሰበር ችሎትበሕግ አውጪው ማሻሻያ ሳይሆን በዳኝነት "አክቲቪዝም" በኩል ወደ የዳበሩ የፍትሕ ሥርዓቶች መፍትሔ እያመራ የሚገኝ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ችሎቱ በውሳኔው ቁልፍ ክፍል ላይ ያስቀመጠው"በቅድመ-ሁኔታ የታጠረ የልዩ ሁኔታ" መብት መርህ ህግ ማውጣትን ያክል የሚቆጠር እንጂ በፍርዱ ትንታኔ/ሀተታ ውስጥ የተጠቀሱት የስነ ስርዓት ህጎቹ ውስጥ ሊገኝ የሚችል ሀረግ/አባባል አይደለም፡፡

በአንዳንድ አገራት ያለው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ሦስተኛ ወገን የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርብበት መብት ተገቢ ነው ያለውን ጊዜ ወስኖ መብቱ የሚከበርበትን መንገድ ክፍት የሚያደርግ መሆኑን ፅሁፎች ያሳያሉ፡፡ እንደዚህ አይነት አካሔድ ከሥነ-ሥርዓት የመጨረሻነት ይልቅ ለመሠረታዊ **እውነት እና ፍትሕ** ቅድሚያ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕግ አውጪ ግን መብቱን "**ከአፈጻጸም በፊት**" በሚል በመገደብ ለፍርድ የመጨረሻነት ትልቅ ቦታ ሰጥቷል፡፡ የሰበር ችሎቱ ግን ሕገ-መንግሥታዊ መርሆዎችን በመጠቀም ይህንን የጊዜ መስኮት ለማስፋት ሞክሯል፡፡ ሌላው በንፅፅር ሊጠቀስ የሚችለው የአገራችን የፍ/ብ/ስ/ስ ሕግ ዋነኛ ምንጭ እንደሆነ የሚጠቀሰው የሕንድ ሕግ ሲሆን የሕንድ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት (Order 21) ሦስተኛ ወገኖችን በፍርድ ለማስገደድ የሚያስችሉ እጅግ ሰፊ የሆኑ የቅድመ-አፈጻጸም ሥርዓቶች እንዳሉት ይነገራል፡፡ በህንድ ስርዓት በክርክር ላይ ያለ ንብረት ማስታወቂያዎች(Notice of Pendency) የሚል ስርዓት/ዶክትሪን ተግባራዊ እንደሚደረግ ፅሁፎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ዶክትሪን አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት ላይ መሆኑን፣ እና ማንኛውም ይህንን ንብረት የሚገዛ ሦስተኛ ወገን የፍርድ ቤቱን የመጨረሻ ውሳኔ ውጤት ለመቀበል ተገዳጅ እንደሚሆን በሚመለከተው የንብረት ማረጋገጫና ምዝገባ ተቋም [Registry] ሰነድ ላይ በግልጽ እንዲሰፍር/እንዲመዘገብ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት የሚደረግ ምዝገባ ተራ ማስታወቂያ አይደለም፡፡ በንጽጽራዊ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ (ለምሳሌ በሕንድ) ይህ ዶክትሪን ሲተገበር፣ አንድ ሰው ንብረቱን ከገዛ በኋላ "በቅን ልቦና የገዛሁ (Bona fide purchaser) ስለሆንኩ ክርክሩን አላውቅም" የሚለውን

መከራከሪያ ሙሉ በሙሉ ያሳጣዋል፡፡ ምክንያቱም ሕጉ፣ ማስታወቂያው በመዝገብ (Registry) ላይ እስካለ ድረስ ገዢው እንደሚያውቅ ግምት (Constructive notice) ውስጧል ማለት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ትልቁ ችግር እንዲህ አይነቱ በክርክር ላይ ያለ ንብረት የመመዝገብ ሥርዓት ግልፅ ህግ የሌለውና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎች ሊከናወን የሚችል ነው ቢባል እንኳን በተቋም ደረጃ የተሳሰረ ሁኖ አይገኝም፡፡ አሁን በተግባር በሰፊው የሚሰራበት አሰራርም ፍርድ ቤቶች ክስ ሲቀርብላቸውና የይከበርልኝ/ይታገድልኝ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ንብረቱን ለማገድ ወደ አግባብነት ወዳለው ተቋም (ለምሳሌ፡ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ወይም የመሬት አስተዳደር) ትዕዛዝ የማስተላልፍ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሂደት አዝጋሚ በመሆኑ እና ሕጋዊ የክርክር ንብረት መዝገብ (Registry) ስለሌለ፣ ንብረቱ ሳይታገድ በፊት ሦስተኛ ወገኖች ሊገዙ የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር ችሎቱ ለምን የሦስተኛ ወገን መብት ጠያቂዎችን "ከአፈጻጸም በኋላ" አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ ለመፍቀድ እንደተገደደ (ይኸውም ይህ መከላከያ ሥርዓት በሀገሪቱ ባለመኖሩ ምክንያት መሆኑን) ለአንባቢው እና ለሕግ ባለሙያው ፍንትው አድርጎ ያሳያል ብሎ መግለፅ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ክርክር መኖሩን ለሕዝብ በግልጽ የሚያሳውቅ ዘመናዊ የምዝገባ ሥርዓት ባለመኖሩ፣ በቅን ልቦና ለሚገዙ ሦስተኛ ወገኖች ሊያውቁት በማይችሉት ፍርድ እንዲገደዱ ማድረግ እጅግ ኢ-ፍትሐዊ መሆኑ ይታመናል፡፡ አዲሱ የሰበር ውሳኔው ችሎቱ በህጉ በተሰጠው የህግ ተርጓሚነት የስልጣን አድማስ ስር የተሰጠ አይደለም የሚል ትችት ሊቀርብበት የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ ከላይ የተጠቀሰውን አስተዳደራዊ እና ሥርዓታዊ ውድቀት (systemic administrative failure) ለማካካስ የሚያስችል የድህረ-አፈጻጸም መተንፈሻ (safety valve) የሰጠ ነው ተብሎ ግን ሊወደስ ይችላል፡፡

<u>፮.ሂሳዊ ምዘና፡- ተግባራዊ ማነቆዎች እና የማስረጃ ሸክም ፈተናዎች</u>

በአካዳሚክ ደረጃ ውሳኔው እጅግ ከፍ ያለ የህግ ትርጉም ዋጋ ያለው ነው ሊባል የሚችል ቢሆንም፣ እንደ ሕግ ባለሙያ (practitioner) በዚህ አዲስ መርህ ውስጥ የተሰወሩ ከባድ ተግባራዊ ፈተናዎችን እንደሚኖሩ ማንሳት ግድ የሚቻል ሁኖ ይታያኛል፡፡ እንዚህም፡-

1. **አለማወቅን (Negative Fact) የማስረዳት ሸክም፡-**

ችሎቱ የማስረዳት ሸክሙን የጣለው በአዲሱ ከሳሽ (ሦስተኛ ወገን) ላይ ሲሆን፣ ከሳሹ ከአፈጻጸም በፊት ስለ ክርክሩ "አያውቅም እንደነበር" ማስረዳት አለበት፡፡ በክርክር ሂደት ውስጥ 'አለማወቅን' ወይም ያልተፈጠረን ነገር (Negative state of mind) ማስረዳት እጅግ ከባድ ከሚባሉ የማስረዳት ሸክሞች አንዱ ነው፡፡ "ማወቅ" ሲባል ምን ማለት ነው? ቀጥተኛ መረጃ መድረስ ነው ወይስ በተዘዋዋሪ ማወቅ መቻል (constructive notice)?፣ ጎረቤቶች ስለ ክርክሩ የሚያውቁ ቢሆን፣ ፍርድ ቤቱ ሦስተኛ ወገኑም ያውቃል ብሎ ይገምታል? ችሎቱ የ**"በቂ ምክንያት"** ድንበሮችን በግልጽ ባለማስቀመጡ፣ ጉዳዩን አደገኛ በሆነ ሁኔታ ለታች ፍርድ ቤት ዳኞች ግላዊ አመለካከት/subjectivity/ አሳልፎ ሰጥቷል፡፡

2. **የ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" (Force Majeure) የተሳሳተ አጠቃቀም፡-**

የችሎቱ ውሳኔ "**ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት**" የሚለውን ሐረግ በግልጽ ተጠቅሟል፡፡ በፍ/ህ/ቁጥር 1792 ድንጋጌ ስር እንደተመለከተው በኢትዮጵያ የሕግ ዶክትሪን ውስጥ "ከአቅም በላይ" የሚባለው እጅግ ጠንካራ መለኪያ ያለው (ለምሳሌ፡ የተፈጥሮ አደጋ፣ ጦርነት ወዘተ) እና አንድን ድርጊት መፈጸም ፈጽሞ የማይቻል የሚያደርግ ክስተት ነው፡፡ ይህንን ጥብቅ መለኪያ በሥነ-ሥርዓት መብት መጓደል ላይ ተግባራዊ ማድረግ እጅግ ከባድ ነው፡፡ አንድ ሦስተኛ ወገን ምንም ዓይነት ጦርነትም ሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ሳይፈጠር፣ በቀላሉ በሌላ ክልል ወይም በውጭ ሀገር ስለሚኖር ብቻ ክርክሩን ላያውቅ ይችላል፡፡ የሕገ-መንግሥት መብቱ በ"ከአቅም በላይ" ጥብቅ ትርጉም እንዳይዋጥ፣ ችሎቱ የበታች ፍርድ ቤቶች "**በቂ ምክንያት**" የሚለውን ሐረግ በሰፊው (liberally) እንዲተረጉሙት የሚያስችል መለኪያ ሊተውላቸው ይገባ ነበር፡፡

3. **በቅን ልቦና በገዙ ወገኖች (Bona fide Purchasers) ላይ የተደቀነ አደጋ፡-**

አንድ ሦስተኛ ወገን የፍርድ ክርክር እንዳለ ሳያውቅ ከአንድ ባለዕዳ ላይ ንብረት ከአፈጻጸም በፊት ቢገዛ፣ ይህ ሰው በቅን ልቦና የገዛ ሦስተኛ ወገን ነው፡፡ በአዲሱ የሰበር ችሎቱ ትርጉም መሠረት፣ ድንገተኛ አፈጻጸም ከመምጣቱ በፊት የመቃወም አቤቱታ ባለማቅረቡ "ከአቅም በላይ" የሆነ ምክንያት ካላቀረበ ንብረቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ይህ በንብረት ገበያው እና በሪል ስቴት ግብይቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የደህንነት ስጋት (insecurity) ይፈጥራል፤ ምክንያቱም ማንም ከሳሽ "**አለማወቁን**" የሚያስረዳ አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ፣ የተፈጸሙ የባለቤትነት ማረጋገጫዎች በማንኛውም ጊዜ የመፍረሽ ሥጋት ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

## ፯. ማጠቃለያ እና መፍትሔዎቹ

በሰ/መ/ቁጥር 236212 የተሰጠው ትርጉም ችሎቱ አዲስ ህግን የማውጣት ያህል የተጓዘበት ታላቅ የዳኝነት ትርጉም ፍልስፍናዊ ውጤት ነው፡፡ ከፍርድ አፈጻጸም በኋላ አዲስ ክስ አይቀርብም የሚለውን ፍጹማዊ ክልከላ በመስበር፣ የሰበር ችሎቱ ፍትሕ የማግኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብት ላይ ህይወት የዘራበት ነው ሊባል የሚችል ትርጉም የያዘ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የንብረት መከበርን (attachment) በሚመለከቱት (ቁ. 418/421/455) ድንጋጌዎች ላይ የነበረውን የተሳሳተ ትርጉም በማረም፣ ጉዳዩን ወደ ትክክለኛው የሦስተኛ ወገን መብት ማዕቀፍ መልሶታል፡፡

ይሁንና የዳኝነት ትርጉም ብቻውን የሕግ አውጪውን ክፍተት ሊደፍን አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ቀልጣፋን ውጤታማ የፍትሐብሔር የፍትሕ አስተዳደር እንዲኖር ወይም በተለይ ከላይ የተገለፀው አዲሱ የህግ ትርጉም አሉታዊ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲተገበር ለማስቻል የሚከተሉት ማሻሻያዎች/ስራዎች ሊሰሩ አለባቸው፡-

- **የሕግ አውጪው ጣልቃ ገብነት፡-** የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን ከዘመኑ ጋር እንዲራመድ በሚያስችል መልኩ ህጉን አጠቃላይ ማሻሻል የሚጠበቅበት መሆኑ እንደተጠበቀ ከላይ ከተነሳው የህግ ትርጉም ጭብጥ አንጻር "ከአፈጻጸም በኋላ ስለሚነሱ የሦስተኛ ወገን መብቶች" የሚገዛ ግልጽ ድንጋጌ በሚሻሻለው ህግ ውስጥ ማካተት አለበት፡፡ በተለይም "**በቂ ምክንያት**" ከሚለው ሰፊ ሐረግ ይልቅ፣ ጥብቅ የሆነ የይርጋ ጊዜ (ለምሳሌ፡ አፈጻጸሙን ከተረዳበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ወይም ሌላ ጊዜ) በሕግ ሊወሰን ይገባል፡፡
- **በክርክር ላይ ያለ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት፡-** የነዚህ ሁሉ ችግሮች መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያሉ ክርክሮች ለሕዝብ በግልጽ የሚታወቁበት ሥርዓት አለመኖሩ ነው፡፡ ምንም እንኳን በፍ/ቤት የሚደረግ ክርክር በግልፅ ችሎት የሚታይ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ያውቀዋል የሚል ጠቅላላ ግምት ቢኖርም ከነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ይህ ግምት ሁልጊዜ የማይሰራ በመሆኑ የተሻለ አመራጭ የንብረት ምዝገባ ሥርዓትን ማዘመን ነው፡፡ እግድ እስካለተሰጠ ድረስ በንብረቱ ማህደር ውስጥ ንብረቱ በክርክር ላይ ያለ መሆኑ የማያታወቅበት ሁኔታ በሰፊው ያለ በመሆኑ ክርክር

እንደተጀመረ በባለቤትነት ካርታው ላይ "**በክርክር ላይ ያለ**" የሚል እገዳ መመዝገብ እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ሊኖር ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት ምዝገባ ስርዓት ሲኖር ማንም ሦስተኛ ወገን ወደፊት መጥቶ "አላወቅኩም" ሊል ስለማይችል፣ ይህ የሥነ-ሥርዓት ቅዠት ሙሉ በሙሉ ይፈታል፡፡

- **የዳኝነት ቢጋር/መምሪያ ማውጣት፡-** የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአፈጻጸም በፊት የመቃወም አቤቱታ ላለማቅረብ "**በቂ ምክንያት**" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚተነትን አስገዳጅ ቢጋር ወይም መመሪያ ለታች ፍርድ ቤቶች ሊያወጣ ይገባል፡፡ ለዚህ ሌላው አማራጭ ሰበር ችሎቱ ሀረጉን ለመተርጎም የሚቻልበትን አግባብ መፈለግ ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ይህም የማስረጃ ሸክሙ መሠረታዊ ፍትሕን የመከልከያ መሣሪያ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

በፍርድ የመጨረሻነት (Finality) እና በፍትሐዊነት (Fairness) መካከል ያለው ሚዛን መቼም ቢሆን ፍጹም ሆኖ አይገኝም፡፡ ነገር ግን ችሎቱ በመ/ቁጥር 236212 የሰጠው አዲሱ ትርጉም በፍትሕ ሚዛን ሳይለኩ ወይም በህጉ አግባብ ሳይሰሙ መብታቸውን የሚነካ ዳኝነት ያረፈባቸው ዜጎች የፍትህ ሚዛኑ ለዘላለም የተዘጋ እንዳይሆን ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችል እሙን ነው፡፡